21 አፕሪል 2021

# ምርጫ 2013 የበይነ መረብ ውይይት

## የመግቢያ ንግግር

ክቡራትና ክቡራን፣

ምርጫ 2013 በፖለቲካ ፓርቲዎች እይታ በሚል ርእስ ያዘጋጀነውን በይነ መረብ ውይይት ለመከታተል ስለተገኛችሁ *በድልድይ* በአውሮፓ የኢትዮጵያዊያን መድረክ ስም ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ድልድይ የፖለቲካ ወገንተኛ ያልሆነ፣ በኢትዮጵያ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና የሰብአዊ መብት አያያዝ ጉዳዮች በልሂቃን መካከል መደማመጥ የሰፈነበት ውይይት በማካሄድ ስለ ሕዝባችን አንድነትና ስለአገራችን ህልውና መሠረተ ሰፊ የጋራ ራዕይ እንዲዳብር ለማገዝ የተቋቋመ መድረክ ነው። ባለፉት ስድስት ዓመታት የሕግ ባለሙያዎችን፣ ኢኮኖሚስቶችን፣ የፖለቲካ ሰዎችን፣ የታሪክ ምሁራንን፣ ዲፕሎማቶችን፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችንና የሲቪል ማህበረሰብ ወኪሎችን ጋብዘን አወያይተናል። የዛሬውንም ወይይት ያዘጋጀነው በዚሁ መንፈስ ነው።

ክቡራትና ክቡራን፣

አገራችን ኢትዮጵያ ፈተና ውስጥ ነች። ከ27 ዓመት የአንድ ፓርቲ አምባገነናዊ አገዛዝ በኋላ በብዙ የአገሪቱ አካባቢዎች እየበረታ የመጣውን ሰላማዊ የሕዝብ አመጽ ተከትሎ በ2010 ዓም ራሱ ገዢው ፓርቲ አገሪቱን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አሸጋግራለሁ በማለት የጀመረውና ሰፊ የሕዝብ ድጋፍና ዓለም አቀፍ እውቅና የተቸረው ለውጥ፣ የተቀነባበረ በሚመስል የውስጥና የውጭ መጠነ ሰፊ ጫና ምክንያት፣ እየተንገዳገደ ነው። በብዙ የአገራችን ክፍል ሰላም ደፍርሷል። ከመተከል እስከ አጣዬ፣ ከቤኒሻንጉል እስከ ጌዴኦና አማሮ ኬሎ፣ ከአጋርፋ እስከ ሻሸመኔና ጂማ፣ ዜጎች ቤብሄር ምንጫቸውና በእምነታቸው ምክንያት ይገደላሉ። ለዘመናት ጸንቶ የኖረውን የህዝቦች ወንድማማችነትና እህትማማችነት ለማላላት የሚደረገው የጽንፈኞች አፍራሽ እንቅስቃሴ ተበራክቷል። ኢትዮጵያን ለ27 ዓመት ቀጥቅጦ የገዛውና እርስበርስ ጥላቻን አውርሶን ከሥልጣን የወረደው ሕወሃት እንደገና ወደ ሥልጣን ለመመለስ በከፈተው ጦርነት የተነሳ የትግራይ ህዝብ ለረሀብ፣ ለስደትና ለመጠነ ሰፊ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ተዳርጓል።

ባጠቃላይ፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አርማ በሆነው በታላቁ ሕዳሴ ግድብ ዙሪያ ከጎረቤት አገሮች ጋር በተፈጠረው ውጥረት፣ በአገራችን በትግራይ በተከሰተው ግጭት እና በመሀል አትዮጵያ በአራቱም ማዕዘን ጽንፈኞች በፈጠሩት ትርምስ ተንተርሰው፣ የውጭ ኃይሎች አገራችን ኢትዮጵያ የራሷን ችግር በራሷ መፍታት የተሳናት በማስመሰል ብሄራዊ ነጻነታችንን ለመድፈር አሰፍስፈዋል።

በዚህ መሃል ነው እንግዲህ የዘንድሮ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ የሚካሄደው። ከሁሉም በላይ ግን፣ ይህንን ሊካሄድ ሰባት ሳምንት ብቻ የቀረውን አገር አቀፍ አጠቀላይ ምርጫ አስመልክቶ በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል በምርጫ በመሳተፍና አለመሳተፍ ጥየቄ ልዩነት ይታያል። በዚህ ጉዳይ የጋራ አመለካከት አለመኖሩ ሁኔታውን ይበልጥ አሳሳቢ ያደርገዋል። ከዚህም የተነሳ፣ ድልድይ በአውሮፓ የኢትዮጵያውያን መድረክ፣ በዚህ ኢትዮጵያ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመሸጋገር በጀመረችው ጉዞ ላይ ከፍተኛ አንደምታ ይኖረዋል ተብሎ በተገመተው ምርጫና ተያያዥ አገራዊ ጉዳዮች ላይ፣ አስተያየታቸውን እንዲያጋሩን ሦስት ግንባር ቀደም የፖለቲካ መሪዎችን ጋብዟል።

እነሱም፤

ፐሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ		የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ ፓርቲ (ኢዜማ) መሪ

ዶክተር መረራ ጉዲና		የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ) ሊቀመንበር

ዶክተር አረጋዊ በርሄ		የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) ሊቀመንበር

ፐሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ፣ ዶክተር መረራ ጉዲና፣ ዶክተር አረጋዊ በርሄ ግብዣችንን ተቀብላችሁ በውይይቱ ለመሳተፍ በመካከላችን ስለተገኛችሁ በድልድይ በአውሮፓ የኢትዮጵያዊያን መድረክ ስም ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

አበራ የማነ አብ